# የአንበጣ መንጋ የአርሶ አደር ወገኖቻችንን የድካም ፍሬ የሆነውን ሰብል እያወደመ ይገኛል

October 10, 2020

**የመረጃ ቲቪ** አባል በመሆን የሳተላይት ቲቪውን ቀጥታ ስርጭት፣ ወቅታዊ ዜናዎችን እና ትንተናዎችን፣ የመዝናኛ ፕሮግራሞችን፣ ስፖርት እና ሌሎችንም ዝግጅቶቻችንን በፍጥነት እና ጥራት ስልክዎ፣ ኮምፒዩተርዎ ወይም ቲቪዎ ላይ ማየት ይችላሉ።



በሃገራችን ለሁለተኛ ጊዜ የተከሰተው የአንበጣ መንጋ የብዙ አርሶአደር ወገኖቻችንን የድካም ፍሬ የሆነውን ሰብል እያወደመ ይገኛል::

ሃገራችን በተፈጥሮ አደጋዎች በተከታታይ እየተፈተነች ትገኛለች:: ሰብሉ ደርሶለት የሚሰበስብበትን ቀናት ለሚጠባበቅ አርሶ አደር በአንድ ጀምበር በአንበጣ መንጋ ሰብሉ ሲወድምበት ማየት እጅግ ያሳዝናል::

ይህ ችግር አርሶ አደሩን ብቻ ሳይሆን ሁላችንንም የሚነካ ችግር ነው:: የፌደራል መንግስቱም፣የክልል መስተዳድሮችም ይህን የአንበጣ መንጋ ለመከላከል ቀጠሮ የማይሰጠው አፋጣኝ እርምጃ በመውሰድ አደጋው ከዚህ የከፋ እንዳይሆን ከፊተኛ ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል::

ህዝቡም እንደ ህዝብ ከወገኖቹ ጎን ከመቆም በተጨማሪ ወደ አላህ ምህረትን በመለመን የመጣብንን ተከታታይ ፈተናዎች በእዝነቱ እንዲመልስልን ልንማፀነው ይገባል::




**ስለ አንበጣው ከሚነገረው በላይ እጅግ አሳዛኝ እየሆነ ነው፣ ገበሬው የሚበላው እህል ብቻ ሳይሆን የእንስሳት ቀለብ የሆነውን አገዳ ጭምር እየበላ ነው። በሰው ሃይል ለማባረር የሚደረገው ርብርብ ጩኸት የጥይት ድምፁን ጨምሮ አእምሮን ይረብሻል፣ ጭሱ ያፍናል። አንበጣው በሚበርበት ግዜ ይማታል… ፀሃይንም ይጋርዳል። ይህ ሁሉ ያልኩት በትክክል በኛ አካባቢ የተከሰተ ሃቅ ስለሆነ ነው። ለሞራል ካልሆነ በተአምር በሰው ሀይል የሚቆም አይደለም፣ ከሰው ሀይል ቁጥጥር ውጪ ነው። ሴቶች በድንጋጤ ፀጉራቸውን ይነጫሉ፣ ይህ ድርጊት በአካባቢያችን ሰው ሲሞት የሚደረግ ክስተት ነው። —**

*አርአያ መንገሻ ከራያ*

*• ዘንድሮ በምስራቅ አፍሪካ በተከሰተው የበረሀ አንበጣ ሳቢያ እጅግ ከፍተኛ የሆነ የሰብል ውድመት እየተከሰተ ይገኛል፣ ይህም ዘንድሮ ከነበረው ከፍተኛ የዝናብ መጠን ጋር ይገናኛል።*

*• በሰሜን ኢትዮጵያ፣ በሱዳን እና ሰሜናዊ ሶማሊያ የነበረው ከመጠን በላይ ዝናብ ችግሩን በዋነኝነት ፈጥሯል፣ ወደፊትም የበረሀ አንበጣው እንዲስፋፋ ጥሩ ሁኔታዎችን ፈጥሯል። እስካሁን የቀጠለው ዝናብ የፈጠራቸው እፅዋት ለአንበጣው መራባት ምክንያት ሆነዋል።*

*• በመጪዎቹ ሳምንታት ለበለጠ መራባት ምቹ የሆኑ ሁኔታዎች በምስራቃዊ ዩጋንዳ፣ በደቡባዊ ደቡብ ሱዳን፣ በሰሜን-ምዕራብ ኢትዮጵያ እና በሰሜን-ምዕራብ ኬንያ ይፈጠራል ተብሎ ይጠበቃል፣ በቀጣይ የንፋስ አቅጣጫ አንበጣውን ወደ ሰሜን አፍሪካ እንደሚወስድ ተገምቷል።*